# ጋዜጣዊ መግለጫ


አሜሪካ ኤምባሲ

አዲስ አበባ ለተጨማሪ መረጃ በ 011-130-7033 ይደውሉ

2013/03 ድረ ገጽ፡ http://ethiopia.usembassy.gov


## የአሜሪካ መንግስት በገጠር ላሉ ስራ ፈጣሪዎች እገዛ የሚያደርግ አዲስ የግብርና አገልግሎት መርሃ ግብር ይፋ አደረገ፤

*በኦሮሚያ የሚቋቋሙ ስድስት የግብርና አገልግሎት ማዕከላት ለአርሶ አደሮች ጥራት ያላቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች በአስተማማኝነት፣ በወቅቱ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባሉ፡፡*

**አዲስ አበባ፣ ጥር 27 ቀን 2005 ዓ.ም.-** የአሜሪካ መንግስት የፕሬዚደንት ኦባማ ፊድ ዘ ፊውቸር-ኢትዮጵያ መርሃግብር አካል የሆነና በአሜሪካ የዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ) የሚመራ የግብርና ንግድ አገልግሎት መርሃ ግብር በዛሬው ዕለት ይፋ አደረገ፡፡ መርሃግብሩ የኢትዮጵያ መንግስት ለሚተገብረው የግብርና ዕድገት ዕቅድ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ አዲሱ የሁለት ዓመት መርሃግብር በገጠር ለሚገኙ ወንዶችና ሴቶች ስራ ፈጣሪዎች ብድርና ስልጠና በመስጠት አንድ የጅምላና ስድስት የችርቻሮ የግብርና አገልግሎት ማዕከላት እንዲያቋቁሙ እገዛ በማድረግ በአካባቢያቸው የሚገኙ አርሶ አደሮችን የዕለት ተዕለት ፍላጎት ለማሟላት እገዛ ያደርጋል፡፡ የግብርና አገልግሎት ማዕከላቱ በኦሮሚያ ክልል 30,000 ለሚሆኑ አርሶ አደሮች አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

የግብርና አገልግሎት ማዕከላት ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ያሉ የጅምላ እና የችርቻሮ አቅራቢዎች ሲሆኑ፤ ማዳበሪያ፣ ዘር፣ የግብርና መሳሪያዎች እና መገልገያዎች ከሚያቀርቧቸው የግብርና ዕቃዎች ወይም ግብዓቶች መካከል ይገኛሉ፡፡ ማዕከላቱ በተጨማሪም እንደ ማሽን ኪራይ፣ የእንስሳት ሕክምና ምክር እና ገበያ ልማት ያሉ ሰፊ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ እያንዳንዱ የግብርና አገልግሎት ማዕከል አርሶ አደሮች ሙያዊ የቴክኒክ ድጋፍ የሚያገኙበት የስልጠና መስጫ ቦታ ይኖረዋል፡፡ ማዕከላቱ አርሶ አደሮች ምርትንና ትርፍን ለመጨመር የሚያግዙ እና ጥራት ያላቸውን ግብዓቶች ለመግዛት እንዲችሉ የብድር አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ግብዓቶች አቅርቦት ዳይሬክተር አቶ ተሾመ ላቀው በመክፈቻ ስነስርዓቱ ላይ ባደረጉት ንግግር "የግብርና አገልግሎት ማዕከላት በስራቸው ለታቀፉ አርሶ አደሮችና ቤተሰቦቻቸው እጅግ ጠቃሚ የሆነ የእሴት ሰንሰለት ለመገንባት ያስችላሉ፡፡ አሰራሮችን እና ጥራት ያላቸውን ግብዓቶች ከማሳወቅ ጀምሮ፤ ከነጋዴዎችና ገበያዎች ጋር ትስስር እስከ መፍጠር የሚያስችሉት እነዚህ ማዕከላት የግብርና ዕድገት ዕቅዳችንን ለማሳካት ጠቀሜታ ያላቸው ሀብቶች ናቸው፡፡" ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የግብርና ንግድ አገልግሎት መርሃግብሩ በማዕከላቱ የሚተዳደርና አገልግሎት የሚሰጥ ፤ብሎም ከአገር ውስጥና ከዓለምአቀፍ አቅራቢዎች ጋር የሚያገናኝ በጅምላ የሚገዛ የሕብረት ስራ ማህበር እንዲቋቋም እገዛ ያደርጋል፡፡ መርሃ ግብሩ የአቅርቦቶችን ተደራሽነት በማሻሻል ምርታማነት እና የግብርና ንግድ ተወዳዳሪነት እንዲጨምር እገዛ ያደርጋል፡፡ ይህ ደግሞ ዘላቂነት ባለውና በግል ሴክተር በሚመራ የግብርና ግብዓት አቅርቦት እና አገልግሎት አማካኝነት የአነስተኛ ባለይዞታዎችን ምርታማነት፣ የምግብ ዋስትና እንዲሁም ገቢ ያሻሽላል፡፡

በአካባቢ ደረጃ በሚኖር ባለቤትነት ላይ የሚያተኩረው ፕሮጀክት፤ የግብርና አገልግሎት ማዕከላት ባለቤቶች ዘላቂ የሆኑ ድርጅቶችን እንዲያቋቁሙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ- ኢትዮጵያ ሚሽን ምክትል ዳይሬክተር ጄሰን ፍሬዘር በንግግራቸው " ዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ እና ለኢትዮጵያ አጠቃላይ ዕድገት እና ብልጽግና አስተዋጽኦ ለማድረግ ጥረት ለሚያደርጉ ትጉህ ስራ ፈጣሪዎች ድጋፍ በማድረጉ ኩራት ይሰማዋል፡፡" ብለዋል፡፡

ይህን የ2 ሚሊዮን ዶላር የዩ ኤስ ኤ አይ ዲ ፕሮጀክት ሲ ኤን ኤፍ ኤ (ቀድሞ ሲቲዝንስ ኔትዎርክ ፎር ፎሬይን አፌየርስ የሚባለው) ይተገብረዋል፡፡

###